መመሪያ ቁጥር 193/2019

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተካሄደባቸው ተቋማት የሚያገለግሉ የሠራተኞች የምደባ አፈጻጸም መመሪያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ለማዘመን፣ የተቋማትን ውጤታማነት ለማሳደግ እና የመንግሥትን ሀብት በቁጠባና በአግባቡ ለመጠቀም ሲባል የሪፎርም እና የመዋቅር ማሻሻያ ጥናቶችን መሠረት በማድረግ የተቋማት የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ ያደረገ በመሆኑ፤

ይህንኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አደረጃጀት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተጀመረውን የሪፎርም እርምጃ ተከትሎ፣ የሰው ኃይልን በአግባቡ በመመደብ ለሕዝቡ የሚሰጠውን የአገልግሎት ጥራት ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ስለሆነም የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚያገለግሉ ሠራተኞችን ሕጋዊ መብትና የሥራ ዋስትና ማረጋገጥ፣ እንዲሁም ሠራተኞቹን ካላቸው የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ ልምድና ችሎታ አንጻር አግባብነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ በፍትሐዊነትና በግልጽነት መልሶ መመደብ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ 94/2019 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሠ) እና የአዲስ አበባ ከተማ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 87/2017 አንቀጽ 152 ንዑስ አንቀጽ (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተካሄደባቸው ተቋማት የሚያገልግሉ የሠራተኞች የምደባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 193/2019" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1/ "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ነው፤

   2/ "ምደባ" ማለት የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው ተቋማት ውስጥ የሚያገለግሉ ሠራተኞችን በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ የመመደብ/የማዛወር ሂደት ነው::

   3/ "ሠራተኛ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 87/2017 የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

   4/ "የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ የተደረገበት ተቋም" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 94/2019 መሠረት ሥልጣንና ተግባሩ ማሻሻያ የተደረገለት አስፈጻሚ ተቋም ነው፤

   5/ "የዓላማ ፈጻሚ ዘርፍ" ማለት የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተካሄደባቸው ተቋማት ውስጥ የመሥሪያ ቤቱን ዋና ተልዕኮና ዓላማ በቀጥታ የሚያስፈጽሙ የሥራ ክፍሎች እና በውስጣቸው የሚያገለግሉ ሠራተኞች ናቸው፤

   6/ "የአስተዳደር ወይም የድጋፍ ሰጪ ዘርፍ" ማለት የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተካሄደባቸው ተቋማት ውስጥ የመሥሪያ ቤቱን ዋና ዓላማና ተልዕኮ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ ድጋፍ ሰጪ ሥራዎችን የሚያከናውኑ የሥራ ክፍሎች እና በውስጣቸው የሚያገለግሉ ሠራተኞች ናቸው፤

   7/ "የምደባ ውድድር መስፈርት" ማለት በአስተባባሪዎች፣ ዳይሬክተሮች፣ የቡድን መሪዎችና ባለሙያዎች/ሠራተኞች ምደባ ወቅት የክፍት የሥራ መደቡ ብዛትና የሠራተኞች ቁጥር አለመመጣጠን (ከመደቡ በላይ ሠራተኛ መኖር) ሲረጋገጥ ሠራተኞችን አወዳድሮ ለመመደብ የሚያስችል አሠራር ነው፤

8/ **"አስፈጻሚ ተቋም"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 94/2019 መሠረት የተቋቋመ የከተማው አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ነው፤

9/ **"የበላይ ኃላፊ"** ማለት የአስፈጻሚ ተቋምን በበላይነት የሚመራ ሰው ነው፤

10/ **"ምደባ ኮሚቴ"** ማለት በየደረጃው ባሉ የአስተዳደሩ አስፈጻሚ ተቋማት የሥራ መደቦች ላይ በተዘጋጀው መስፈርት መሠረት ሠራተኞችን በውድድር ወይም ያለ ውድድር ምደባ በማዘጋጀት የውሣኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ ነው፤

11/ **"ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ"** ማለት የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተካሄደባቸው አስፈጻሚ ተቋማት በተካሄደ ምደባ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚመረምርና የውሣኔ ኃሣብ ለበላይ ኃላፊ የሚያቀርብ ነው፤

12/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

13/ በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል።

3. **<u>የመመሪያው ዓላማ</u>**

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1/ የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው ተቋማት የሚገኙ ሠራተኞችን የአገልግሎት አሰጣጥ ሳይስተጓጎል አግባብ ባላቸው ሌሎች ተቋማት ውስጥ በፍትሐዊነት መመደብ፤

2/ የዓላማ ፈጻሚ ዘርፍ ሠራተኞችን ቀድመው ይሠሩት የነበረው የሥራ ዘርፍ ወይም ተልዕኮ በተሰጠው ወይም ወደተላለፈበት አዲሱ መሥሪያ ቤት አብረው እንዲዛወሩ ማድረግ፤

3/ የድጋፍ ሰጪ ዘርፍ ሠራተኞችን በሌሎች የመንግሥት ተቋማት ባሉ ክፍት የሥራ መደቦችና የመሥሪያ ቤቶችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ በቢሮው በኩል ምደባ እንዲያገኙ ማድረግ።

4. **<u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ እና የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚያገለግሉ ቋሚ የመንግሥት ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የአደረጃጀት ለውጥ ስለተደረገባቸው ተቋማት እና የሠራተኞች ምደባ

5. የአደረጃጀት ለውጥ የተደረገባቸው ተቋማት እና የሠራተኞች ምደባ ሁኔታ

የተቋማት አደረጃጀት እና የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያን ተከተሎ የሠራተኞች ምደባ በሚከተለው ሠንጠረዥ መሠረት ይፈጸማል፦

ተራ ቁ	ነባር የተቋሙ መጠሪያ	አዲሱ የተደራጀበት የተቋም መጠሪያ	አዲስ ወደተደራጀበት ተቋም ምደባ የሚሰጣቸው ሰራተኞች
1	ሥራና ክህሎት ቢሮ	የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ቢሮ	ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ፣ ኢንዱስትሪ አክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስር ያሉ ሰራተኞች ብቻ ይሆናል።
		የሰራተኛና የስራ እድል ፈጠራ ቢሮ	ቴክኒክና ሙያ ቢሮ ምደባ ከሚያገኙት ውጪ ቀሪዎቹ የአስተዳደር ዘርፍ ሰራተኞችን ጨምሮ በነበሩበት የሚቀጥሉ ይሆናል፣
2	የመስሪያ ቦታዎች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ	የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ	በመዋቅራዊ ጥናት መነሻ ምደባ ይከናወናል፣
		የሠራተኛና የሥራ እድል ፈጠራ ቢሮ	
3	የምግብና መድሀኒት ቁጥጥር ባለስልጣን	ጤና ቢሮ	ጤና ቢሮ/ የጤና ባለሙያዎችና የጤና ተቋማት ዳይሬክቶሬት እና የሕግ፣ የህክምና ስህተት ጤና ባለሙያዎች ሥነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት ላይ ሲያገለግሉ የነበሩ ሠራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
4	ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን	የትራንስፖርት ቢሮ	የትራፊክ ቁጥጥር፣ የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ፣ የፓርኪንግ አስተዳደር ሥራዎችላይ ሲያገለግሉ የነበሩ ሠራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
		መንገዶች ባለስልጣን	የመንገድ ደህንነት ኢንጂነሪንግና አፕሬሽን ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣

ተራ ቁ	ነባር የተቋሙ መጠሪያ	አዲሱ የተደራጀበት የተቋም መጠሪያ	አዲስ ወደተደራጀበት ተቋም ምደባ የሚሰጣቸው ሰራተኞች
		የትራፊክ ማኔጅመንት ማእከል	የመቆጣጠሪያ ማእከል ሥራዎች ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
5	ቱሪዝም ኮሚሽን ባህልና ኪነጥበብ ቢሮ	የባህልና ቱሪዝም ቢሮ	የቱሪዝም ኮሚሽን ዓላማ ፈጻሚ ሠራተኞች ብቻ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ይመደባሉ፣ የባህልና ኪነጥበብ ሠራተኞች አስተዳደር ዘርፉን ጨምሮ በነበሩበት ይቀጥላል፣
6	ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ	የህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባባሪያ ኮሚሽን	በበጎ ፈቃድ ስራዎች ዳይሬክቶሬት ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
7	ትምህርትና ስልጠና ቁጥጥር ባለስልጣን	ለትምህርት ቢሮ	ከአጠቃላይ ትምህርት እውቅና ፈቃድና እድሳት፣ ከአሰራር ጥራት የአጠቃላይ ትምህርት ቁጥጥር ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
		ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ቢሮ	የቴክኒክና ሙያ እውቅና ፈቃድና እድሳት፣ ከአሰራር ጥራት የቴክኒክና ሙያ ቁጥጥር ላይ የሚገኙ ሰራተኞች [illegible]
8	ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን	ፋይናንስ ቢሮ	የንብረት ኦዲትና ኢንስፔክሽን ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
		የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ	የህንጻና ምድረ ግቢ ደህንነት አገልግሎት፣ የህንጻ አስተዳደር ጥናት እና የንብረት ስታንዳርዳይዜሽን ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
		ዲዛንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ	የመንግስት ህንጻ ልማት
9	አመራር አካዳሚ	የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ	የስልጠና ምርምር እና የማማከር ዳይሬክቶሬት ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ
		የመንግስት ሠራተኞች ብቃት ምዘና ማረጋገጫ ተቋም	የመንግስት ሠራተኞች ብቃት ዘርፍ እና አስተዳደር ዘርፍ ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
11	ህብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ አስተባባሪ ኮሚሽን	የሰላምና ፀጥታ ቢሮ	የሰላም ሰራዊት አደራጅ ባለሙያ ብቻ ይመደባሉ፣

ተራ ቁ	ነባር የተቋሙ መጠሪያ	አዲሱ የተደራጀበት የተቋም መጠሪያ	አዲስ ወደተደራጀበት ተቋም ምደባ የሚሰጣቸው ሰራተኞች
12	የመንግስት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር ባለስልጣን	ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ኮርፖሬሽን	የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የነበሩ ሰራተኞች የሚመደቡ ይሆናል
13	የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ	ስትራቴጂያዊና ልዩ ኢንሼቲቭ ፕሮጀክት አስተዳደር ጽ/ቤት	የትላልቅ ፕሮጀክቶች ዘርፍ ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
14	ምገባ ኤጀንሲ	ትምህርት ቢሮ	የተማሪዎች ምገባ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች ብቻ ይመደባሉ፣
		የህጻናት ማህበራዊና ሴቶች ጉዳዮች	የተስፋ ብርሀን የምገባ ማእከል ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ብቻ ይመደባሉ
15	ፋይናንስ ቢሮ	ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ኮርፖሬሽን፣	- -----
16	የቴያትር ቤቶች አስተዳደር ሲኒማ ቤቶች አስተዳደር	የቴያትርና ሲኒማ ቤቶች አስተዳደር	የቴያትርና ሲኒማ ቤቶች አስተዳደር ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ይመደባሉ፣

6. **<u>የሠራተኞች የምደባ አፈጻጸም</u>**

ሀ) የዓላማ ፈጻሚ ሰራተኞች ምደባ በተመለከተ፡-

1/ **የሠራተኛ ምደባ የሚካሄደው በተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው ተቋማት ውስጥ ባሉ የሥራ መደቦች ላይ ብቻ ይሆናል፤**

2/ **የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ሠራተኞች ሕጉን መሠረት በማድረግ እንደ አዲስ ወደተደራጁባቸው ተቋማት ምደባ እንዲያገኙ ይደረጋል፤**

3/ **በተቋሙ ዕቅድ መሠረት መሥሪያ ቤቱ ፈቅዶለት አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ በሚፈጅ ትምህርት ወይም ሥልጠና ላይ የሚገኝ ሠራተኛ በዚህ ምደባ ውስጥ አይካተትም፤**

4/ **ማንኛውም ሠራተኛ የሥራ መደቡን ተፈላጊ ችሎታ መሠረት በማድረግ በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ ላይ ብቻ ምደባ እንዲሰጠው ይደረጋል፤**

5/ **በተከለሰው አደረጃጀት ላይ የሥራ መደቡ ብዛትና የሠራተኛው ቁጥር የተለያየ (ያልተመጣጠነ) ከሆነ ምደባ የሚሰጠው በውድድር ይሆናል፤**

6/ **የኮንትራት ወይም ጊዜያዊ ቅጥር ሠራተኛን የሠራተኛ ድልድል በሚካሄድባቸው የሥራ መደቦች ላይ ማወዳደርም ሆነ መመደብ የተከለከለ ነው፤**

7/ በትውስት፣ በጊዜያዊነት፣ በውክልና ወይም በተጠባባቂነት በማገልገል ላይ የነበሩ ሠራተኞች በቋሚነት ተመድበው ወደነበሩበት የሥራ መደብ እንዲመለሱ ይደረጋል፤

8/ በቀላል ወይም በከባድ የዲሲፕሊን ክስ ተመስርቶባቸው ጉዳያቸው በመታየት ላይ ያሉ ሠራተኞችን ከምደባ ውጭ አያደርጋቸውም፤ ሆኖም በሂደት ላይ የሚገኘው ጉዳይ መታየቱ ይቀጥላል፤

9/ በዲሲፕሊን ውሳኔ ከነበረው ደረጃና ደመወዝ ዝቅ እንዲል የተደረገ ሠራተኛ በዚህ ምደባ የቅጣት ጊዜውን እስከሚያጠናቅቅ ድረስ ዝቅ ባለበት ደረጃ ላይ ይመደባል፤

10/ በእስር ላይ የሚገኝ የመንግሥት ሠራተኛ በዚህ ምደባ ውስጥ የሚሳተፍ አይሆንም፤

11/ በእንደገና ማደራጀት አሠራር ምደባ ያልተገኘለት ሠራተኛ ሲያጋጥም በሚመጥነው የሥራ መደብ ወደ ሌሎች ተቋማት እንዲመደብ ይደረጋል፤

12/ በምደባ ወቅት በመሥሪያ ቤቱ ዕውቅና በሥራ ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ በሰው ሀብት አስተዳደር መረጃ አቅራቢነት ምደባው እንዲፈጸም ይደረጋል፤

13/ የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ ሥራው የተላለፈለት መሥሪያ ቤት የተመደቡለትን ሠራተኞች የመቀበልና በአዲሱ መዋቅር ውስጥ የማካተት ግዴታ አለበት።

ለ) የድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ምደባን በተመለከተ፡-

በአስተዳደር ሥራ ክፍሎች ላይ ከሚገኙ ሠራተኞች መካከል ከአመራር አካዳሚ እና ከሠራተኛና ሥራ ዕድል ፈጠራ ቢሮ በስተቀር፣ ሁሉም የአስተዳደር ዘርፍ ሠራተኞች በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ በኩል በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ምደባ እንዲያገኙ ይደረጋል።

7. <u>የምደባ መስፈርት</u>

የዳይሬክተሮች/ቡድን መሪዎች ባለሙያዎች ወይም ሠራተኞች የማወዳደሪያ መስፈርትና የተሰጣቸው ክብደት በሚከተለው አግባብ የሚተገበር ሆኖ የሥራ መደቡና የሠራተኛው ቁጥር መለያየቱ ሲረጋገጥ ብቻ የሚፈፀም ይሆናል፡-

ተ.ቁ	የመመዘኛ መስፈርቶች	የማወዳደሪያ ነጥብ (ከ100%)	ምርመራ
1	የትምህርት ዝግጅት የሚሰጥ ነጥብ	10	ፒኤችዲ/10/፣ማስተር/8/፣ የመጀመሪያ ዲግሪ/6/
2	የስራ ልምድ	10	ከ10 ዓመት በላይ ያገለገለ/10/፣ ከ5-10 ያገለገለ /8/ እና ከ5 በታች 6፣
3	የስራ አፈጻጸም ምዘና አማካኝ ውጤት / የ2018 የሁለቱ	70	የጸደቀውን የሥራ አፈጻጸም ውጤት ብቻ መሰረት ያደረገ

	መንፈቅ ዓመት/		ይሆናል፣
4	የበላይ ሀላፊ	5	
4	የማህደር ጥራት	5	
	ጠቅላላ ድምር	100	

8. **<u>የምደባ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>**

የምደባ ኮሚቴ የሚቋቋመው የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው አስፈጻሚ ተቋማት ላይ ሆኖ የሰው ሀብት የሥራ ክፍል ባላቸው መሥሪያ ቤቶች ላይ ይሆናል።

9. **<u>የምደባ ኮሚቴ አወቃቀር</u>**

የምደባ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1/ በበላይ ኃላፊ የሚሰየም ---------- ሰብሳቢ፣

2/ በበላይ ኃላፊ የሚሰየም አንድ ባለሙያ ---------- አባል፣

3/ የአደረጃጀት ለውጥ ከተደረገባቸው ሠራተኞች የሚወከሉ ሁለት ሠራተኞች (ቢያንስ አንዱ ሴት የሆነች) ---------- አባል፣

4/ ከሰው ሀብት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወይም ተወካይ...አባልና ጸሐፊ።

10. **<u>የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>**

የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቋቋመው የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ በተደረገባቸው አስፈጻሚ ተቋማት ላይ ሆኖ የሰው ሀብት የሥራ ክፍል ባላቸው መሥሪያ ቤቶች ላይ ይሆናል።

11. **<u>የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አወቃቀር</u>**

የቅሬታ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1/ በበላይ ኃላፊ የሚሰየም ---------- ሰብሳቢ፣

2/ በበላይ ኃላፊ የሚሰየም አንድ ባለሙያ---------- አባል፣

3/ አደረጃጀት ለውጥ ካደረጉ ሠራተኞች የሚወከሉ አንድ ---------- አባል፣

12. **<u>የአስፈጻሚ ተቋማት ኃላፊነት</u>**

እያንዳንዱ አስፈፃሚ ተቋም የሚከተሉት ኃላፊቶች አሉበት፡-

1/ ለምደባ የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አደራጅቶ ለምደባ ዝግጁ ማድረግ፤

2/ በተደረገው የተግባርና ኃላፊነት ማሻሻያ ላይ ለሠራተኞች ግንዛቤ መፍጠር፤

3/ ማንኛውም ሠራተኛ ምደባ እስኪሰጠው ድረስ በነበረበት መሥሪያ ቤት በሥራ ሰዓት እንዲገኝ የማድረግና የክትትል ሥራ ማከናውን፤

4/ የሠራተኞችን የግል ማኅደር እና ተያያዥ መረጃዎችን በአግባቡ አደራጅቶ ለሚመለከተው አካል የማስረከብ፤

5/ የተመደቡላቸውን ሠራተኞች በአዲሱ የሥራ መደብ ላይ በፍጥነት የመመደብ፣ የሥራ መመሪያ የመስጠትና አስፈላጊውን የሥራ ቁሳቁስ የማሟላት።

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. **የተከለከለ ተግባር**

1/ ውድድር በሚኖርበት ጊዜ የሥራ አፈጻጸም ምዘና በአዲስ መልክ እንዲሞላ ማድረግ የተከለከለ ነው።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የሥራ መደቡ ብዛትና የሠራተኛው ቁጥር ባለመመጣጠኑ ምክንያት በሚኖረው ውድድር ላይ በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ምደባ ያላገኙ ሠራተኞች ሲኖሩ ከሁለት ደረጃ ባልበለጠ የሥራ መደብ ላይ ዝቅ አድርጎ መመደብ ይቻላል።

14. **ተፈፃሚት የሌላቸው ሕጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም ቢሮው ያወጣው መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

15. **መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በቢሮው ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ፣ ጥቅምት 2 ቀን 2019

ጥላሁን ከበደ

በምክትል ከንቲባ ማእረግ የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ